**የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን**
**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣**
**ክቡራትና ክቡራን፤**

በኢትዮጵያ ረጅም የመንግሥት አስተዳደር ዘመን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ግልጽና ተአማኒ ምርጫ በማካሄድ፣ ሕዝባዊ ቅቡልነትን ያገኘ መንግሥት በምንመሠርትበት ታሪካዊ ቀን፣ ከፊታችሁ ቆሜ ንግግር ለማድረግ ያበቃኝን ፈጣሪ ከሁሉ አስቀድሜ ለማመስገን እወዳለሁ።

በዚህ ወሳኝና ፈታኝ ወቅት በሀገራችንና በሕዝቦቿ ላይ የተቃጣውን የህልውና አደጋ ለመቀልበስ፣ በዱር በገደሉ፤ በቁር በሐሩሩ፣ ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረጉ ለሚገኙት - ለጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን፣ ለመላው የጸጥታ አካላት እና ለሕዝባዊ ኃይላችን ያለኝን ታላቅ አክብሮትና ምስጋና ልገልጽ እወዳለሁ። እናንተ የቁርጥ ቀን ልጆች፣ ጀግና የምታከብረው ኢትዮጵያ ውለታችሁን መቼም ቢሆን አትረሳውም። ሀገራችን እንደቀደሙ ጀግኖቿ ለዚህ ትውልድ ፈርጦችም ትልቅ ክብርና ሞገስ ትሰጣለች። የምትከፍሉት መሥዋዕትነት በታሪክ ማኅደር እና በልባችን ብራና ላይ በደማቁ ታትሞ ይኖራል።

እልፍ ጀግኖችን ካፈራው ሕዝባችን አብራክ በመፈጠሬ ሁሌም እንድኮራ ከሚያደርጉኝ ነገሮች መካከል - የሕዝባችን ጽናት፥ አይበገሬነት እና አትንኩኝ ባይነት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

ሕዝባችን በየትኛውም ዘመን የእናት ሀገሩ ጥቃት የሚያንገበግበው፣ ጠላት ሲመጣ የግል ቅሬታውን ወደ ጎን ብሎ ሀገርን የሚያስቀድም፣ በሉዓላዊነቱ የማይደራደር ነው፡፡ በዚህም የተነሣ መተማመኛችን፥ ጦርና ጋሻችን፥ ተዋጊና ደጀናችን ለሆነው ሕዝባችን ያለኝን ክብርና አድናቆት ልገልጽ እውዳለሁ። በተመሳሳይ፣ ኢትዮጵያ ድጋፍ በፈለገች ጊዜ ለደረሳችሁላት፣ ዐቅምባነሳት ጊዜ ምርኩዝ ለሆናችኋት፣ በመላው ዓለም ለምትኖሩ ኢትዮጵያውንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ - በሕዝብና በመንግሥት ስም የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

ኢትዮጵያ - በአቃፊነቷና በቀደመ ገናና ታሪኳ በመርከብ ትመሰላለች። በታላላቆቹ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደተነገረው፣ መርከቧ ኢትዮጵያ - የፍትሕ፣ የእኩልነት፣ የነጻነት እና የላቀ ሰብእና ሀገር ናት። እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ "ነብር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ መልኩን አይቀይርም" የተባለልን ነን፡፡ ከቀደምት ክርስቲያኖች መካከል አንዱ የሆነው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባን ያፈራን ነን፤ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተከታዮቻቸው ማረፊያ አድርገው የመረጧት፤ የእውነትና የርትዕ ሀገር ብለው ያወደሷት እና የመጀመሪያው ሙዓዚን የቢላል መነሻ የሆነች ሀገር ናት ኢትዮጵያ። እኛ ማለት የመካከለኛው ዘመን ፖርቱጋላዊ አሳሽና ጸሐፊ ፔድሮ አልቫሬስ "ኢትዮጵያውያን ፍትሕና ዳኝነትን የሚያውቁ፣ ኪነ ሕንጻ እና ሥዕሎቻቸው በጥበብ የደመቁ" ሲል የመሰከረልን ሕዝቦች ነን፤ ኢትዮጵያ በኤዞቅ ተረቶችና በሜናንደር ተውኔቶች የተወደሰች ናት፣ የታሪክ አባት ሄሮዶተስ "የወርቃማ ባህልና ሥነ ምግባር ባለቤት የሆኑ ብልሕ ሕዝቦች" ብሎ የጻፈላት፤ የዘመናችን አርኪዖሎጅስቶች ምድረ ቀደምትነቷን ያረጋገጡላት ፤ ኢትዮጵያ በነ ማርከስ ጋርቬይ እና ዱቦይስ ልቡና ውስጥ ጎልታ የተሳለች ፤ በፀረ ቅኝ ግዛትና ፀረ አፓርታይድ ትግል ወቅት ከራሷ አልፋ፣ ለአፍሪካ ነጻነት ከውስን ሀብቷ ሳትሰስት ቀርሳ የሰጠች፤ በማንዴላ ውብ ቃላት "አፍሪካዊ ማንነቴን የገለጠችልኝ" ተብላ የተወደሰች፤ የእውነትና የአፍሪካዊነት ሞገስ ነች ኢትዮጵያ።

አንዳንዶች ዛሬ "አትችሉም" ሲሉን መቻላችንን፤ አንድም - ከታሪክ መዝገብ ገልጠን የአባቶቻችንን ገድል በማሳየት፣ ሁለትም - የእኛ ትውልድ ለኢትዮጵያ ብልጽግና የወጠነውን እና አይቀሬውን የተግባር ጉዞ ልናሳይ ይገባል። ስለ አለፈ ዘመናችን ስንናገር ከሚሰማን ኩራት ጋር ሲነጻጸር፣ ነገ የሚጠብቀን ተስፋ ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ዋናው ጥያቄ - ተስፋውን አይተን እውን ለማድረግ ምን ያህል ቁርጠኞች ነን? የሚለው ነው። ኢትዮጵያ የምትበለጽገው እኛ ለመለወጥ በፈለግንበት መጠንና የጋራ ራዕይ በሰነቅንበት ልክ ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ካዘመመችበት ቀና የምትልበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ይኼን ለማሳካት የዛሬ ህያው ኢትዮጵያውያን ታላቅ አደራ ተጥሎብናል።

ይኼንን አደራ ጠብቀን፤ የዘመናት በጎ ድምር ውጤቶችን አጎልብተን፣ ኢትዮጵያ የተባለችውን መርከብ ሞተሯን አድሰን፣ ማዕበልና ወጀብ ፈጽሞ እንዳያናጋት አድርገን፣ መልሕቋን አንሥተን፣ ጉዞዋን ማስጀመር የእኛ ድርሻ ነው፤ ለዘለቄታው በጽናት እንድትጓዝ ማድረግ ደግሞ የየትውልዱ አደራ ይሆናል።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

ሀገራችን፣ ላለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት ዴሞክራሲን በሥርዓተ መንግሥቷ ለመትከል ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጋለች። ተስፋና ሥጋት፥ ዕድልና ፈተና እየተፈራረቁባት አያሌ ውጣ ውረዶችን ተሻግራ እዚህ ደርሳለች። የማንነት፣ የእኩልነት፣ የነጻነት እና የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጥያቄ - ከአርሶ አደር እስከ አርብቶ አደር፣ ከከተሜ እስከ ባላገር፣ ከመለዮ ለባሽ እስከ ምሁር፣ ከወጣት እስከ ጎልማሳ፣ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ፣ መላው የሀገራችን ሕዝቦች የተሳተፉበትና መሥዋዕትነት የከፈሉበት የዘመናት የሕዝብ ጥያቄ ነበር።

ምንም እንኳን 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ከእንከኖች ሁሉ የጸዳና የምኞታችንን ያህል እጅግ የተሳካ ነበር ባይባልም፣ የዘመናት ጥያቄ የነበረውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የመትከል እና የማጽናት ሕልም እውን ለማድረግ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል፤ አንድ ርምጃም ወደፊት አራምዶናል። ሥልጣን በዘር ሐረግ ወይም በጠመንጃ አፈሙዝ፣ አልያም በሤራና በተንኮል ሳይሆን፤ በእውነተኛ የሕዝብ ድምፅ ከምርጫ ኮሮጆ ብቻ የሚመነጭ በማድረግ፤ የሕዝብን የፖለቲካ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤትነት ካረጋገጥንበት ዘመን ላይ ደርሰናል።

ሕዝባችን - የዕንቅፋት ክምር ሳያስቆመው፣ በጊዜያዊ ፈተና ተስፋ ሳይቆርጥ፣ በልዩ ልዩ ሰው ሠራሽ ግጭቶች ሳይረበሽ፣ እንደ ኮቪድ ወረርሽኝ ባሉ ተፈጥሯዊ አደጋዎች ሳይበገር፣ በሀገራዊ ሉዓላዊነታችን ላይ በተጋረጠው አደጋ ሳይረታ፣ በውጭ ኃይሎች ለሚደርስበት ተጽዕኖ ሳይንበረከክ፣ በሂደቱ የገጠሙትን እንከኖች ሁሉ ተጋፍጦ፣ የዜግነት ድርሻውን አኩሪ በሆነ መልኩ ተወጥቷል።

**ውድ የሀገሬ ልጆች**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

በምርጫው የተመዘገበው ድል የአንድ ፓርቲ ብቻ አይደለም፤ የመንግሥትም ብቻ አይደለም። ድሉ - ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ በአንድነት ያሸነፍንበት ነው፡፡ ይሄን አጋጣሚ እንደ ሀገር በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ካዋልነው ብዙ ቀዳዳዎችን መድፈን የሚያስችል ትልቅ ዕድል ነው። ለዘመናት እየተከማቹ የመጡትን የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ችግሮች፣ በአንድ ፓርቲ መሪነት እና መፍትሔ አፍላቂነት ጨርሶ ማስወገድ እንደማይቻል መታወቅ አለበት፡፡ ከዚያ ይልቅ ተደራርበው የመጡብንን ችግሮች ተባብረን እና ተደምረን ለማሸነፍ መነሳት ይኖርብናል። በእኛ በኩል - በሁሉም፣ ከሁሉም፣ ለሁሉም የሆነች ኢትዮጵያን የመገንባት ሕልም ለስኬት እንዲበቃ - አሳታፊና አካታች አካሄድ ለመከተል አጥብቀን እንሠራለን።

የፖለቲካ ሥርዓታችን የአሸናፊዎች ፍላጎት ነጸብራቅ ብቻ ሳይሆን የመግባባታችን ውጤት እንዲሆን አበክረን እንሠራለን። በታሪካችን ውስጥ በጉልህ እንደሚታየው፣ የውስጥ ሽኩቻዎቻችን ለጠላቶቻችን መሳለቂያና መረማመጃ አድርገውን ቆይተዋል። የኦሮሞ አባቶች “Waliigalan alaa galan” ይላሉ። “የተግባባ ከውጪ ይገባ፤ የተነጋገረና የመከረ ለአንገብጋቢ ችግሮቹ መፍትሔ ያገኛል” እንደማለት ነው።

መጪው ዘመን ብዝኃነታችንን በጌጥነት ተቀብለን፣ መታረቅ የሚችል ሐሳባችንን አስታርቀን፣ መከበር የሚገባው ልዩነታችንን አክብረን፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን አጠንክረን፣ ወደ ከፍታ የምንትምበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ይህም እንዲሳካ የፖለቲካ ልዩነታችንን ለማጥበብ አካታች ብሔራዊ የውይይት መድረክ እናካሂዳለን። የምክክር ሂደቱ ችግሮቻችን በጠረጴዛ ዙሪያ ይፈታሉ ብለው የሚያምኑትን የሚያካትት ነው፡፡

ምክክሩ በፖለቲካ ልሂቃን መካከል የሚደረግ ሂደት ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ያገናዘበ ይሆናል፡፡ አጠቃላይ ሂደቱ አካታችና አሳታፊ፤ እንዲሁም በኢትዮጵያውያን እየተመራ ሀገር በቀል መፍትሔዎችን ለማፍለቅ ታልሞ ይከናወናል።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በክህደት እና በዕብሪት የተጠነሰሰው ግጭት፣ ባሳለፍነው ዓመት እንደ ሀገር እጅግ ከባድ ዋጋ አስከፍሎናል። ይህ ግጭት ጥቂት ግለሰቦች ‹እኛ የማንቆጣጠራት እና እንዳሻን የማናሾራት ሀገር ልትኖር አይገባም› ብለው የቀሰቀሱት ጦርነት ነው። ጠላት በአሸከሮቹና በአሳዳሪዎቹ እየታገዘ፣ ብረት አንሥቶና አውዳሚ መሣሪያዎችን ታጥቆ፤ እንደ ብሌናችን በምንሳሳለት የሰሜን ዕዝ ሠራዊት ላይ የግፍ ግፍ ፈጽሟል።

በቅርቡ እንኳን የጥሞና ዕድል ብንሰጠው፣ ክፉ ደጉን ያልለዩ ሕፃናትን የጦር መሣሪያ አስታጥቆ፣ የሕዝብ መገልገያዎችን እየናደ፤ ትምህርት ቤትና ጤና ኬላዎችን እያፈረሰ፤ ቤተሰብ እየበተነ፤ ንጹሐንን እየረሸነ፤ አርሶ አደሩ ከልጆቹ ለይቶ የማያያቸውን ከብቶቹን በጥይት እየገደለ፤ የሃይማኖት ተቋማትን እያረከሰ፣ ኢትዮጵያን ሲወጋት፣ ወደን ሳይሆን ተገደን ህልውናችንን ወደ ማስጠበቅ ዘመቻ መግባታችን ሊታወቅ ይገባል።

ሰልፍ ይዘን ስንዘምትም ሆነ ሰይፍ ይዘን ስንነሣ፣ ዋና ጠባችን ሀገር ሊያፈርሱ፥ ሕዝብ ሊያናክሱ፥ ወንበራቸውን ሊያደላድሉ፥ ኪሳቸውን ሊሞሉ ከተነሡ የሤራ ቁንጮዎች እና ከኢትዮጵያ-ጠል ኃይሎች ጋር ብቻ ነው። ሀገራችን ከውጭና ከውስጥ የገጠሟትን ፈተናዎች ተቋቁማ ለማለፍ እና በቀጣይም ብሔራዊ ክብሯንና ጥቅሟን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስከበር እንድትችል ትክክለኛ አቋም እና የተሟላ ዐቅም ያለው የጸጥታና የደኅንነት ኃይል ትገነባለች።

**ክቡራትና ክቡራን**

ሉዓላዊነታችንን እና የግዛት አንድነታችንን የሚገዳደረውን ክፉ መሻት በምንከላከልበት በዚህ ወቅት ከዓለም አቀፍ ኃይሎች እያስተናገድን ያለው የዲፕሎማሲ አዝማሚያ ወደኋላ መለስ ብለን ታሪካችንን እንድንገልጥ አስገድዶናል።

በዘመናት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችን ውስጥ ሁለት ተቃራኒ ሐቆችን አሳልፈናል። ዛሬም እንደ ትናንቱ የወዳጅነትን ታሪክ የቀጠሉ እንዳሉ ሁሉ፣ የክህደትን ታሪክ የደገሙም አሉ። ኢትዮጵያ ወደ ብልጽግና ለምታደርገው ጉዞ የወዳጆቿን አጋርነት አጥብቃ ትሻለች። ነገር ግን ማንኛውም ወዳጅነት የኢትዮጵያን ክብርና ሉዓላዊነት በሚሠዋ መልኩ መሆን የለበትም፤ ሊሆንም አይችልም።
በፍቅር መንፈስ ለሚቀርቡን ሀገራት፣ ልባችንና በራችን - ለድጋፋቸው፣ ለምክራቸውና ለመልካም ምኞታቸው ሁሌም ክፍት ነው።

**ውድ አፍሪካዊ እኅቶቻችን እና ወንድሞቻችን፣**

እኛ ኢትዮጵያውያን "ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ" በሚል መርሕ የተባበረች፣ ሰላማዊትና የበለጸገች አፍሪካን ለመገንባት ብሎም፣ በዓለም መድረክ ጥቅሟን የምታስጠብቅ አህጉር እንድትኖረን፣ ከመቼውም ጊዜ በላይ ኃላፊነታችንን ለመወጣት እንጥራለን።

በቀጣናችን - ከሚያጋጩን ይልቅ የሚያስታርቁን፣ ከሚያለያዩን ይልቅ የሚያስተባብሩን ነገሮች ብዙ ናቸው። የጋሞ አባቶች "ከሰው ጋር አንድ ዓመት ያላረሰ፤ ለብቻው ሰባት ዓመት ያርሳል" እንዲሉ፤ ዕጣ ፈንታችን የተሣሠረ ስለሆነ፣ በቀጣናችን ያለውን የተበታተነ ዐቅም ሰብሰብ አድርገን ብንተባበር፣ ያሉብን ችግሮች "በንሥር ፊት እንደቆመች ድንቢጥ" ይኮሰምናሉ።

**ክቡራትና ክቡራን፣**

የሕዳሴ ግድብ እንደ ሀገር ከሚያስገኝልን ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ባሻገር፣ ቀጣናዊ ትሥሥር እና መልካም ጉርብትናን የሚያጠናክር ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የዓባይ ወንዝ ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳነቱ ባለፈ ተምሳሌታዊ ትርጉሙ ግዙፍ ነው። ዓባይ ማለት - የመነሣታችን ምሳሌ፣ በራሳችን ዐቅም የመቆማችን ማሳያ፣ የኅብረታችን ገመድ ነው። ዓባይ በማይታይ ምትሐቱ ስላስተሣሠረን፣ በማይዳሰስ ኃይሉ ስላበረታንና በራስ መተማመናችንን ስለጨመረ ከሕፃናት እስከ አረጋውያን፣ ከከተማ እስከ ገጠር፣ ከቆላ እስከ ደጋ፣ ከደቡብ እስከ ሰሜን፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከዕለት ጉርሱና ከመንፈቅ ልብሱ ቀንሶ ግድቡን ለማጠናቀቅ ቆርጧል።

ጎረቤቶቻችንና የዓባይ ልጆች ይኼንን ሐቃችንን እስከተረዳችሁልን ድረስ፣ በዓባይ ወንዝ የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ፣ ቀጣናዊ ትሥሥርን በሚያጠናክር እና ሁሉንም አሸናፊ በሚያደርግ መንገድ ለመሥራት ሁሌም ዝግጁ ነን።

**ውድ የሀገሬ ልጆች፣**

ሀገራችንን ወደ ብልጽግና ጎዳና የማሸጋገር ውጥናችንን ወደ ውጤት ለመቀየር ኢኮኖሚያችን በብዝኃ ዘርፎች የተዋቀረ፣ ብዝኃ ተዋናይ የሚሳተፍበትና እና ብዙዎችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ እንሠራለን። ኢኮኖሚያችን በግል ዘርፍ ቀዳሚነትና ገበያን በሚደግፍ መንግሥት አጋዥነት የሚመራ፣ ተወዳዳሪ እና ከዓለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት ጋር የተሣሠረ፣ ፈጣንና ፍትሐዊ ዕድገትን የሚያረጋግጥ፣ ለዜጎቻችን በቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ምጣኔ ሀብት እንዲሆን እንሠራለን።

ባለፉት ዓመታት የዋጋ ንረትን ከመቆጣጠርና የኑሮ ውድነትን ከመቀነስ አንፃር የተወሰዱት ርምጃዎች የሚፈለገውን ውጤት እንዳላመጡ እና ድሃው የኅብረተሰብ ክፍል የችግሩ ገፈት ቀማሽ መሆኑን መንግሥት በውል ይገነዘባል። ይህንን የኅብረተሰብ ክፍል ከጫና ለመታደግ፣ በሚቀጥሉት ዓመታት መንግሥት የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሠራቸው የኢኮኖሚ አስተዳደር ሥራዎች መካከል አንዱ የዋጋ ንረትን መግራት ይሆናል።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

የምናልመውና እንደ ግብ የምናስቀምጣቸው በጎ ዓላማዎች ትርጉም የሚኖራቸው ባለን የማስፈጸምና የማድረግ ዐቅም ነው። አዲሱ መንግሥት የሚያስብ፣ የሚያቅድ፣ የሚከውን እንጂ፤ በጎ የሚመኝ፥ ሕልመኛ ብቻ ሊሆን አይገባም። እስከዛሬ ታቅደው ከጠረጴዛ ላይ ያልወረዱና ተጀምረው የተሰናከሉ ውጥኖቻችን ባለንበት የምንረግጥ እና አንዳንዴም ወደ ኋላ የምንንሸራተት አድርገውናል።

በዜጎቻችን ላይ የሚደርስን ምሬት እና መንገላታትን ለመቅረፍ፤ ጀምሮ የመጨረስ ባህልን በመላበስ፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ ግልጽና ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ እና ምቹ የሕዝብ አስተዳደር እንዲኖር አበክረን እንሠራለን። በተለይ በተለይ ሌብነትን እንደ ቀላል ድክመት ሳይሆን እንደ ከፍተኛ የደኅንነትና የህልውና አደጋ በማየት፣ በቀጣይ ዓመታት ትልቅ ትኩረት ሰጥተን እንሠራበታለን።

**ውድ የሀገሬ ልጆች፣**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

ባሳለፍነው የለውጥ ጉዞ አያሌ ስኬቶች የነበሩ ቢሆንም በርካታ ፈተናዎች አጋጥመዋል። ፍትሕ ከሰፈነ ዕርቃናቸውን የሚቀሩ፤ ዴሞክራሲ ከተተከለ እስትንፋስ የማይኖራቸው፣ እኩልነት ጭቆና የሚመስላቸው፤ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ግለሰብና ቡድኖች አሁንም በሀገራችን ይገኛሉ፤ ወደፊትም በብልጽግና ጉዟችን ውስጥ ሊደቅኑት የሚችሉት ፈተና ጨርሶ እንደማይጠፋ ልንገነዘብ ይገባል። ባለፉት ድሎቻችን ላይ አከማችተን፥ ስሕተቶችን አርመን፥ በአዳዲስ ሐሳብ፣ በአዳዲስ እይታ፣ ትውልዱን የሚመጥን አካሄድ፣ ዘመኑን የሚዋጅ ቅኝት ይዘን፣ ለመጭው ትውልድ የተሻለ ሀገር ለማስረከብ ተደምረን እንተጋለን።

የምናመጣው ለውጥ ተቋማዊ መደላድልና ሕዝባዊ መሠረት ያለው እንዲሆን ስንሠራም ሆነ ለለውጥ ስንቀሳቀስ፣ ዓላማችን በጎ ቢሆንም አልፎ አልፎ ማጥፋትና መሳታችን አይቀርም። ሁሌም እንከን የለሽ ሥራ እንሠራለን የሚል መታበይ የለንም። ነገር ግን ከእኛ በኋላ የሚመጡት እኛ የሳትነውን እንደሚያርሙ፣ የጀመርነውን እንደሚያጎለብቱ ሙሉ እምነትና ተስፋ አለን። ቀጣዮቹ አምስት ዓመታት፣ ባሳለፍነው የለውጥ ጉዞ የታዩ መልካም እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉበትና ፍሬ የሚያፈሩበት ዘመን ይሆናል። በመጭዎቹ ዓመታት ዐቅማችንን በሚገባ ተጠቅመን አንድነታችንን የሚፈታተነውን ጥላቻ ለማስወገድ እንታገላለን፡፡

እንደ ኅዳር አህያ ሀብት ያለው ሁሉ የፈለግኩትን ካልጫንኳችሁ እያለ እንዲመኝ ያደረገውን ድህነታችንን እና ለጠላት ተጋላጭ የሚያደርገንን የውስጥ እና የውጭ ሁኔታ ተገዳድረን ድል ለማድረግ እንተጋለን። ጥላቻን በመግባባት፣ ጭቆናን በዴሞክራሲ፣ ድህነትን በብልጽግና፣ ለጠላት ተጋላጭነታችንን በጠንካራ ብሔራዊ የጸጥታ ኃይል ለመተካት ሁላችንም መረባረብ አለብን።

**የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን**
**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣**
**ክቡራትና ክቡራን፤**

በመጨረሻም
መጪዎቹ ዓመታት - "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም ከአይበገሬነት ጋር የተሣሠረ መሆኑን የምናስመሰክርበት እንደሚሆን አልጠራጠርም። ፈተናዎች መስፈንጠሪያ እንጂ መታሠሪያ አይሆኑብንም። መጭዎቹ ዓመታት - ኢትዮጵያ ሰንኮፏን የምትነቅልበት፣ ቁስሏን የምታክምበት፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነቷን በዐለት ላይ የምታጸናበት፣ ገናናው ስሟ በሰፊው ዓለም የሚናኝበት ዘመን ይሆናል። በመጪዎቹ ዓመታት - የድህነት አከርካሪ፣ የጥላቻ አንገት፣ የመከፋፈል ወገብ፣ የመፈናቀል ወሽመጥ፣ የመገዳደል ክንድ፣ በከንቱ የመወነጃጀል ጉልበት፣ በሀገር ልጆች ብርቱ ትብብር ይሰበራሉ። አባቶቻችን "Akka duriifi harka xuriitti hin hafan" የቆሸሸ እጅና የትናንት ደካማ ማንነት መጥራቱ አይቀርም" እንደሚሉት፣ ፈተናዎች እንደ ወርቅ አንጥረው ያበሯት ሀገር፤ የአቧራው ብዛትና የቆሻሻው ክምር ወርቅነቷን የማይለውጧት ኢትዮጵያ ትናንት ነበረች፤ ዛሬም አለች። ነገ አቧራውን አራግፋና የቆሻሻውን ክምር ንዳ ስትነሣ ያኔ ከፊቷ የሚቆም ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል አይኖርም። ለዚህ ደግሞ አደራ አለብን። ዝናቡና ብርዱ ሳይበግራቸው፣ ቁርና ፀሐይ ሳያማርራቸው፣ በሌሊት እንቅልፍ ሳይሰንፉ፤

ኢትዮጵያን ከመረጡ ዜጎቻችን የተሰጠን አደራ፤ ለኢትዮጵያ መዳን ሲሉ ደማቸውን ካፈሰሱ፣ ሕይወታቸውን ከገበሩ ውድ የሀገር ልጆች የተጣለብን አደራ፤ ሌት ተቀን ስለ ኢትዮጵያ ሰላም በዕንባ የሚማልዱ እናቶች የሰጡን አዳራ፡፡ እንዲሁም፤ ከወዝና ከላባቸው በጨለፉት ትጋት ሀገር ከሚያገለግሉ እናትና አባቶች የተላለፈልን አደራ፤ እኛን ተስፋ አድርገው በኮልታፋ አንደበታቸው ስለ ኢትዮጵያ ከሚዘምሩ ልጆቻችን የተሰጠን አደራ አለብን። አዎ! ከባድ አደራ አለብን። ስለዚህም በቀጣይ ዓመታት የተጣለብንን አደራ ለመጠበቅና በላቀ ብቃት ለማስፈጸም እንደማናንቀላፋ፣ ያለንን ሁሉ ያለስስት እንደምንሰጥ፣ ለአፍታም እንደማንዘናጋ፣ በዚህ አጋጣሚ ቃላችንን እንደምናድስ፤ በመንግሥታችንና በፓርቲያችን ስም በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። አትጠራጠሩ - በቀጣዩ ዓመታት ተስፋችንን አጎልብተን፣ ሥጋቶችን ቀርፈን፣ ዕድሎችን አሟጠን፣ ፈታኞቻችንን አሸንፈን፣ ሀገራችንን በብልጽግና ጎዳና የምናስኬድበት ዘመን ይሆናል።

**ኢትዮጵያ በልጇቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ!**
**Galaatomaa!!!**